# የመደመር መንግሥት ምስረታ

- መስከረም 25 ቀን 2019 ዓ.ም



ኢትዮጵያ

አዲሲቷ የተስፋ አድማስ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) መስከረም 25 ቀን 2019 ዓ.ም የመደመር መንግሥት ምስረታን አስመልክቶ ያስተላለፉት መልዕክት



**የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣**
**የተከበራችሁ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፣**
**ውድ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣**

ከሁሉ አስቀድሜ፣ የዴሞክራሲ እስትንፋስ የሆነውን ምርጫ አካሂደን፣ መንግሥት በምንመሠርትበት በዚህ ታሪካዊ ዕለት - ይህንን ንግግር ለማቅረብ ዳግም ዕድሉን ስላገኘሁ፣ ፈጣሪን እንዳመሰግን ይፈቀድልኝ። በመቀጠልም፣ በሕጋዊ ምርጫ እምነት ጥለው፣ በድምጻቸው ቅቡል መንግሥት ለማጽናት፣ በተግባር ለታመኑ 54 ሚሊዮን ዜጎቻችን፣ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ።

ወርቅ በእሳት እንደሚፈተነው ሁሉ፥ የዴሞክራሲ ባህልም የሚፈተነው በምርጫ ወቅት ነው። ያሳለፍነው ምርጫ፣ እንደ ማንኛውም ሕዝባዊ ምርጫ፣ "ተካሄደ" ተብሎ ብቻ የሚገለጽ፣ የሠርክ ኩነት አልነበረም። ዜጋው በቀላሉ አልመረጠም። ፍቃዱን ሊሰጥ የቻለው በብዙ ውዥንብሮች መሐል አልፎ ነበር።

**በየጫካው እየሸመቁበት፤**
**በየሚዲያው እያዋከቡት፤**
**በአሉባልታ እያስፈራሩት፤**

በብዙ ተግዳሮቶች መሐል፤ ህልውናውን ለማጽናት ሕዝቡ ፈቅዶ መርጧል። አጠቃላይ ሂደቱ፣ የዴሞክራሲ ባህላችን መሠረቱ እየጠነከረ መምጣቱን በግልጽ አሳይቷል። ወደፊት ታሪክ በደማቅ ብዕር እንደሚጽፈው፤ ትውልድም ደጋግሞ እንደሚዘክረው ጥርጥር የለኝም። ማንኛውም ሕዝባዊ ምርጫ፣ አሸናፊና ተሸናፊ ፓርቲ ሊኖረው ይችላል። ኢትዮጵያ ግን፣ አሸናፊ እንጂ ተሸናፊ ዜጋ እንደማይኖራት፣ በዚሁ አጋጣሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ኦሮሞ ሲተርት "Harka tokkoon manni hin ijaaramu" ይላል፣ ቤት በአንድ እጅ አይገነባም እንደማለት ነው። እንደ ሀገር፣ የሚጠብቀንን ፈተና መሻገር የምንችለውም፣ እንደ ወንድማማች፣ ተያይዘን እኩል መራመድ ስንችል ብቻ ነው።

ዛሬ ዘመኑ ተቀይሯል፤ ነገሮች እንደ ድሮ አይደሉም። ሀገራዊ፣ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች በፍጥነት ይለዋወጣሉ። ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ወዲህ የዓለም ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ መልኮች በፈጣን ለውጥ ውስጥ ይገኛሉ። የከርሰ ምድር እንቅስቃሴ ምድሪቱን እየናጠ፤ ሜዳውን ወደ ተራራ ፣ ኮረብታውን ወደ ሸለቆ፣ ባሕሩን ወደ ውቅያኖስ እየለዋወጠ፤ አዲስ ቅርጽና መልክ ያስይዛታል። በተመሳሳይ መልኩ ዓለምም፣ በጂኦ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎቿ ምክንያት መልክና ጠባይዋ ተቀያይሯል። አይገመቴነት የዘመኑ ዋነኛ መገለጫ እየሆነ ነው። ቋሚ አሰላለፍ ማየት ብርቅ ሆኗል።

የባለ ብዙ ዋልታ ዓለም፣ ሊወለድ በሚታገልበት በዚህ ወቅት፣ ጎራ መርጦ ማን ይቆማል? ማንም! የትኛው ፖለቲካዊ ዕሳቤስ፣ በዓለም ላይ እንደሚነግሥ፣ ከግምት በዘለለ፣ በእርግጠኝነት ማን መናገር ይችላል? ማንም! ምን ዓይነት የኢኮኖሚ አካሄድ የቀጣዩ ዓለም ሥርዓት እንደሚሆንስ በውል ተለይቷል? በፍጹም! ጥቁርና ነጩ ያለየለት፣ ግራጫ የፖለቲካና ኢኮኖሚ ዐውድ ውስጥ እንገኛለን። ታሪክ፣ ወደየትኛው አዲስ ምዕራፍ እንደሚያደርሰን በግልጽ በማይታወቅበት፣ መንታ መንገድ ላይ መሆናችን አሙን ነው። አዲስ ነገር ዕዳም ምንዳም አለው። ዕዳና ምንዳው ግን ለሁሉም እኩል አይደለም።



እዚህ ላይ **“ዝግጁነት የድል አድራጊዎች ቁልፍ ናት”** ሲል አሜሪካዊው ጀነራል ዳግላስ መካርተር፣ የተናገረውን ማስታወስ ተገቢ ነው። መጪውን ዘመን ቀድመው አስበው የሚያመጣውን አዲስ ነገር ከወዲሁ ገምተው፣ በተጠንቀቅ ለሚጠብቁ ብርቱዎች ምንዳው ብዙ ነው። በአንጻሩ፣ ዘግተውና ተዘናግተው ለሚቆዩ ደካሞች፣ ዕዳው እልፍ ነው። የሀገራችን አርሶ አደርም “መጪው ክረምት የሚጠቅመው ላረሰው ገበሬ ነው” ይላል። ከሁለቱ አማራጮች ለሀገራችን የሚበጀውን መንገድ መርጦ መከተል፣ የዚህ ትውልድ ትልቁ አደራ ይሆናል።

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣**
**ውድ ኢትዮጵያውያን፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

ዓለም ተከታታይ የኢንዱስትሪ አብዮቶችን አካሂዳለች። በወቅቱ ለነበሩ አብዮቶች ራሳቸውን አዘጋጅተው የተገኙ ሀገሮች፣ አንድም የአብዮቶቹ ተዋንያን ነበሩ፤ አለያም ቶሎ ተነሥተው ተከታዮች መሆን ችለዋል። እኛ ግን፣ በወቅቱ ተዘግተንም ተዘናግተንም ስለነበረ፤ ከኢንዱስትሪ አብዮቶቹ የደረሰን፣ ገፈቱና ትራፊው ነው።

ዓለም ቀዳሚውን የኢንዱስትሪ አብዮት ሲያካሂድ፣ እኛ በዘመነ መሳፍንት ሽኩቻ ውስጥ ነበርን። የእርስ በእርስ ግጭቱ፣ ብዙ ነገሮችን አሳጣን። እኛ ከጦርነት አዙሪት ሳንወጣ፣ ሌላው ዓለም ሁለተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት አስተናገደ። በዚህም ዐቅሙንና ጉልበቱን አደርጅቶ፣ የአውሮፓ ኃይል፣ ቅኝ ሊገዛን ሲመጣ፤ ግማሽ ጉልበታችን በገዛ እጃችን ተገዝግዞ ነበር። በጊዜ ተዘጋጅተን ቢሆን ኖሮ፣ በቀላሉ መመከት ስንችል፣ ዐቅማችንን ጨርሰን ለመጋፈጥ ተገደድን። **ጥያቄው፣ ዛሬስ የት ላይ ነን? የሚለው ነው።**

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣**
**ክቡራትና ክቡራን፣**

በአንድ ዕንቅፋት አንዴ መመታት ተፈጥሯዊ ቢሆንም፣ ደጋግሞ መመታት ግን የጤና አይደለም። እንደ ሀገር፣ ቀድሞ አለመዘጋጀት፣ የሚያስከፍለውን ዋጋ ለማየት፣ የጣልያን ዳግም ወረራን መለስ ብሎ መቃኘት፣ ተገቢና ጠቃሚ ነው። በዐድዋ ጦርነት አንገቱን ደፍቶ የተመለሰው ወራሪ ኃይል፣ አራት ዐሠርት ዓመታትን ያሳለፈው፣ አንገት ቀና በሚያደርግ ዝግጅት ነበር። በአንጻሩ እኛ ግን፣ ከዐድዋ ድል ማግሥት አሸልበን ቆየን። ጊዜውን ጠብቆ፣ ጠላትም መጣ፤ ማይጨው ላይ ከተተ። ያልተቀየረ ቁመና ይዘን፣ የተቀየረውን ዓለም ለመግጠም፣ እኛም ወደ ማይጨው አመራን። በአግባቡ ሳንሰናዳ፣ እስኪበቃው ከተሰናዳ ኃይል ፊት ቆምን።

የሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት፣ ትሩፋት ከሆኑት፣ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ጋር ተጋፈጥን። እኛ በምድር ስንጓዝ፣ ጠላታችን በሰማይ መጣ። ጠላት 450 ዘመናዊ አውሮፕላኖችን ይዞ ሲመጣ፤ እኛ ከ12 በማይበልጡ ወታደራዊ ባልሆኑ አነስተኛ አውሮፕላኖችን ገጠምነው። ለዚህም ነበር ዐርበኞቹ በቁጭት፦

**በትግራይ ቢመጣ መች ይገባ ነበር፣**
**በጎንደር ቢመጣ መች ይገባ ነበር፣**
**በአሰብስ ቢመጣ መች ይገባ ነበር፣**
**በሰማይ መጣ እንጂ በማናውቀው ሀገር፣**

ሲሉ የተደመጡት። ባልተዘጋጁበት ግንባር እንደመግጠም ያለ ክፉ ቀን የለም። የከፋው ቀን ተመልሶ እንዳይመጣ፣ ዛሬም ደግመን እንጠይቃለን።

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ፣
## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት

ዛሬስ፤ ኢትዮጵያ ምን ያህል ተዘጋጅታለች?
ካለፉት ስሕተቶቻችን ምን ያህል ተምረናል?
አንዳችን የሌላችንን እንከን መንቀስ ትተን፣ ዓይናችን ምን ያህል ወደ ውጭ ያማትራል?

ከትናንት በስቲያ በምድር ያገኘነውን ባላንጣ፣ ትናንት በሰማይ ሲመጣ የተገረምን ሕዝቦች፣ ነገ ጠላት በየት በኩል ሊጎበኘን እንደሚችል፣ አስበንና ገምተን ምን ያህል ዝግጁ ሆነናል? ቀጣናችን እየተቀየረ ነው። ጎረቤቶቻችን፤ የአፍሪካ ቀንድ፤ የቀይ ባሕር ከባቢ፤ የፋርስ ባሕረ ሰላጤ፤ የአውሮፓ ጂኦ ፖለቲካ፤ የመካከለኛው ምሥራቅ አካሄድ፤ ሁሉም በየአቅጣጫው በለውጥ ማዕበል እየተጎበኘ ነው። እኛ ደግሞ በአስገራሚውና በአስፈላጊው የዓለም ክፍል ላይ እንገኛለን። ምሥራቅ አፍሪካ፣ ቀይ ባሕርና የሕንድ ውቅያኖስ በሚገናኙበት ልዩ ሥፍራ ላይ መቀመጥ ፈተናም ዕድልም አለው።

የዓለም የነዳጅ ምርት መተላለፊያ የሆነው ባብኤል መንደብ በእኛ ቀጣና መገኘቱ አንድምታው ብዙ ነው። ከኢንዱስትሪ አብዮቶች ዘመን ጀምሮ፣ የታላላቅ ኃያላን መራኮቻ በሆነው፣ በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ መገኘት፣ ምን ማለት እንደሆነ ለመገንዘብ፣ ብዙ ማሰላሰል አይጠይቅም። ናይጀርያውያን ሲተርቱ **“ዝናብ ጣሪያ ለይቶ አይዘንብም”** ይላሉ። በዚህ ቀጣና የሚነሣ የለውጥ ዝናብም፣ እኛን ሳያገኝ ያልፋል ማለት ዘበት ነው።

ፈለግንም አልፈለግንም፤ የዚህ ከባቢ ለውጥ እኛንም ይጎበኘናል። ለዚህም ታሪክ ምስክር ነው። ድሮ ድሮ፣ ይህ አካባቢ በባቢሎናውያንና ፋርሶች፤ በግሪኮችና በሮማውያን፤ በፖርቱጋሎችና በቱርኮች፤ በእንግሊዞችና በፈረንሳውያን ተጽዕኖ ሥር ሲገባ ዕዳውና ምንዳው እኛንም ነካክቶናል። የኃያላኑ ሽኩቻ በተደጋጋሚ ቀጣናውን ቀይሮታል፤ የሀገራችንንም ቅርጽ ወስኖታል። ነጻነታችንን ለማስከበር ስንል፣ ትኩረታችን ከልማት ወደ ጦርነት እንዲዞር አድርጎታል። የባሕር በር ተጋሪነታችን የተለወጠው የተጽዕኖ አድማሳችን ሲኮሰምን የኖረው ፈልገን ብቻ አይደለም፤ ተገደን ጭምር ነው።

ዛሬም፣ ያለንበት ጂኦ ፖለቲካዊ ሁኔታ በፍጥነት እየተለዋወጠ ነው። በዚህ ውጥንቅጥ ውስጥ ጠንክረን መጋፈጥ ከቻልን፣ እንደምናሸንፍ እናምናለን። ደክመን ከተገኘንም ሽንፈት አይቀርልንም። ዐቅም በነበረን ወቅት፣ የራሳችንን ጉዳይ ራሳችን ወስነናል። **በተዳከምን ጊዜ ግና፣ ሌሎች በእኛ ላይ ወስነውብናል።** በተዘጋጀንባቸው ዘመናት፣ ከቀይ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ፤ ከሜዲትራንያን እስከ አትላንቲክ ተጉዘናል። ባልተዘጋጀንበት ወቅት ደግሞ መውጫ-መግቢያ በራችን ተዘግቶብናል። ዓለም አዲስ ቅርጽና መልክ ለመያዝ እየታገለች ነው። በዚህ ጊዜ ቶሎ የነቁና፣ ድርጁ ዐቅም የገነቡ አካላት ማሸነፋቸው አይቀሬ ነው። እኛም ይሄንን አዲስ ምክር ቤት የምንጀምረው፤ ቀጣናችን በዚህ የለውጥ ነፋስ እየተመታ ባለበት ወቅት ነው። እናም በማዕበል የምትናጥ ዓለም ውስጥ እስከ ምን ለመጓዝ ተዘጋጅተናል? በመብረቁ ሳንሸበር፤ በነጎድጓዱ ሳንበረግግ፤ የሚዶፈውን ዝናብ ተቋቁመን፣ ምን ያህል እንቀዝፋለን? ለሚሉት ጥያቄዎች ምላሹ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ይሆናል።

## የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣
## የተከበራችሁ የሀገራችን ሕዝቦች፣



የሁለት ሺህ ዐሥሩን ለውጥ ያመጣው በአዲሱ ትውልድ ውስጥ ያለው ዓለምን አሸንፎ የመጓዝ ፍላጎት ነበር። ለብዙ ተደጋጋሚ ጊዜያት፣ የኢትዮጵያን ለውጦች የሚገፋቸው **"ቁጭት"** ነበር። ሀገር ወደኋላ ስትቀርና፣ ዓለም ወደፊት ሲራመድ፣ የሚፈጠር ቁጭት።

**"ይነዳል ይቆጫል እንደ እግር እሳት ወደፊት ሲሄዱ ከኋላ መቅረት።"** የተባለውኮ በምክንያት ነበር። ከባዱ ነገር ደግሞ ይሄን ቁጭት በተገቢው ሥርዓት የማስተናገድ ፈተና ነው። ቁጭት መነሻ እንጂ፥ ማድረሻም፣ መዳረሻም አይሆንም። ማድረሻው ሥርዓት ሲሆን፣ መዳረሻው ደግሞ ሥልጣኔ ነው። ቁጭት ሥርዓትን እንዲወልድ ሰክኖ ማሰብን ይፈልጋል። ማሰብ፣ ማሰላሰል፣ መመርመር፣ መሞከር፣ የተሻለውን መምረጥና ማሻሻል፤ እነዚህ ሥርዓትን የሚገነቡ ቅመሞች ናቸው። "ሥርዓት" በአንድ ጀንበር ተገንብቶ አያልቅምና። ይልቁንም "ሥርዓት" በሂደት የሚፈጠር፤ ትዕግሥትና ትጋትን እኩል የሚጠይቅ፤ ጥበብና ስክነትን አጣምሮ የያዘ ነገር ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ፣ ሥርዓትን የመገንባት ሙከራዎች፣ የቁጭት ችግር አልነበረባቸውም። በአንድ በኩል የእፎይታና የስክነት ችግር ይስተዋልባቸዋል። በሌላ በኩል ለአዲስ ሐሳብ ዝግ የመሆን ጠባይም በሰፊው ይስተዋላል። ነባራዊውን ዓለም ተገንዝቦ፣ ለኢትዮጵያ የሚሆነውን አዋጪ መንገድ መርጦ፤ ያንን መንገድ ፈትኖና አረጋግጦ፤ ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችል እፎይታና ዝግጁነት ያንሳል። በዚህ ምክንያት የየወቅቱ መሪዎች ከሚያዋጣው መንገድ ይልቅ አቋራጩን ሲመርጡ ኖረዋል። የሀገራችንን ችግር፣ ለሌሎች ተቀዶ በተሰፋ የውጭ ሀገር ዕሳቤ ሊፈቱ ይጣደፋሉ። ከባሕር ማዶ የገለበጡትን ርዕዮተ ዓለም፣ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ካልበቀልክ ይሉታል።

ብዝኃነትን ከአንድነት፤ የእምነት ልዩነትን ከዕሴት ትሥሥር፤ አካባቢያዊነትን ከሀገር፤ የግል ፍላጎትን ከቡድን፤ ትናንትን ከዛሬ፤ ዐቅምን ከአቋም ደምረው ስለሚጓዙ ነው። እኛም ይሄንኑ መንገድ ብንከተል ያዋጣናል ብለን አምነናል። የዓለም ሁኔታም ያስተማረን ይሄንኑ ነው። የአውሮፓ ሥልጣኔ የተገነባው በአውሮፓዊ ባህል ላይ ተመሥርቶ፤ በግሪክ ፍልስፍና ተቃኝቶ፣ በሮማውያን የሥነ መንግሥትነት ዘይቤ ተቀርጾ ነው። የምሥራቅ እስያ ሥልጣኔም የተገነባው ለእስያዊ ባህል በተስማማው በኮንፊሺየስ ዕሳቤ ላይ ተመሥርቶ ነው። ሁለቱም ሥልጣኔዎች ዋናውን ጥንስስ ራሳቸው ጠንስሰው፤ ሌላውን ግብአት ቀምሰውና አጣጥመው፤ ከሚፈልጉት ጣዕም ጋር መስማማቱን እርግጠኛ ሲሆኑ ከሌሎች ወስደዋል።

## እኛስ?

ተመሳሳዩን መርሕ እንዳንከተል ምን ያግደናል? ያለንን የሥልጣኔ ወረት ይዘን፤ የሥነ መንግሥትነት ዕሴታችንን አዘምነን፤ በሀገር በቀል ዕሳቤ ላይ የታነጸ፣ ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔ እንዳንገነባ የሚከለክለን ማነው? ማንም፤ በትውልድ ቅብብሎሽ የደለበውን ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ወረት ፈልፍለን፤ ከባሕር ማዶ የምናገኛቸውን ጠቃሚ ጥበቦች ከኢትዮጵያዊ ዕሳቤ ጋር እንዲጣጣሙ አድርገን፤ በጎደለ ሞልተን ጠንካራ ሥልጣኔ መገንባት እንችላለን። ለሌሎች ዕሳቤ ኢትዮጵያን ከመቀየር ይልቅ፤ ለኢትዮጵያ ሲባል የሌሎችን ዕሳቤ አቃንቶ መቀበል ተገቢ አካሄድ ነው። ባለፉት ዓመታት ስንሞክር፤ ስናርም፣ ስናስተካክል፤ የሌሎችን ተሞክሮ ከራሳችን ጋር ስናስማማ ቆይተናል። መደመር የኢትዮጵያን ሥልጣኔ የማሰቢያ ቋንቋ መሆን እንደሚችል አረጋግጠናል።

የምንኮራባቸው ሥልጣኔዎቻችን ሁሉ በመደመር ዕሳቤ የተቃኙ እንደነበሩ ዐውቀናል። በዚህም ተመሥርተን በለውጡ ጊዜ የሞከርናቸው ተግባራት አስደናቂ ውጤት አምጥተውልናል። ከፋፋይና ጠቅላይ ዕሳቤዎችን፣ በኅብረ ብሔራዊ አንድነት እንዲተኩ ያደረግነው ሙከራ፣ ፍሬ ማፍራት ጀምሯል። **ዳርና መሐል፣ ዋናና አጋር** ብሎ የተከፋፈለውን የፖለቲካ መልክ፣ በመደመር ዕሳቤ፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነት ወዳለው የፓርቲ መዋቅር ቀይረናል።

ትናንትን እንደ ጥራጊ፣ ዛሬን እንደ ብቸኛ አስፈላጊ፤
ወይም ትናንትን እንደ ቅዱስ፣ ዛሬን እንደ ርኩስ ከሚቆጥረው ዕሳቤ ወጥተናል። በምትኩም ከትናንቱ መልካሙን ወስደን፤ ዛሬ አስፈላጊ ዕሴት ጨምረን፤ ለነገ የምናሻግርበትን የታሪክ አተያይ ገንብተናል። በተለመደው የኢኮኖሚ ዕድገት አተያይ፣ ፈጣን ለውጥ እንደማይመጣ ተገንዝበናል። ዕንቁላሎችን በአንድ ቅርጫት እንደማስቀመጥ ካለ የአንድ ዘርፍ አካሄድ ወጥተን፣ ወደ ብዝኃ ዘርፍ ተሸጋግረናል።

ዘመኑ ተቀይሯል፣ የቆመህ ጠብቀኝ ዘመን ተለውጦ፣ በአንድ ጊዜ ብዙ ዒላማዎችን መምታት ከሚቻልበት ዘመን ላይ ደርሰናል። እኛም በተቀናጀ ሥርዓት የሚመራ ብዝኃ ዘርፍ የኢኮኖሚ አካሄድን መከተልን መርጠናል። ያለፉትን ስብራቶች መርምረን፣ በፍጥነትና በፈጠራ መንገድ ራሳችንን ሪፎርም አድርገን፣ የሚመጣውን ዓለም ለመቃኘት እየተዘጋጀን ነው።

በማክሮ ኢኮኖሚ፣ በጸጥታ ዘርፍ፣ በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በኢነርጂ፣ በውጭ ግንኙነት፣ ወዘተ. የጀመርናቸው ሪፎርሞች ፍሬ ማፍራት ጀምረዋል።ኢትዮጵያን ለአዲሱ ዘመን ንቁና ብቁ ለማድረግ የጀመርናቸው የዲጂታል ኢትዮጵያ ጉዞዎች፣ ሀገራችን የአዲሱን ዓለም ጎርፍ ዋኝታ እንድትሻር ብቻ አላስቻሏትም። በአንፃሩ የመዋኛውንም ሁኔታ እንድትወስን ዐቅም እየፈጠሩላት ነው። በዲጂታል ፋይናንስ፣ በዲጂታል ገበያ፣ በዲጂታል አገልግሎት፣ በዲጂታል መታወቂያ፣ በሰው ሠራሽ አስተውሎት እና በዲጂታል መድረኮች ግንባታ የሄድንባቸው ርቀቶች - ነገን ለመዋጀት የሚያስችሉ መሠረቶች ናቸው። የመንግሥት የልማት ተቋማት ኪሣራ መለያቸው፣ ዕዳ መገለጫቸው ነበሩ። ዛሬ ያንን አስቸጋሪ ሁኔታ ተሻግረውታል። የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ የኢትዮጵያን አንጡራ ሀብቶች ሰብስቦ፣ አስተካክሎና አሻሽሎ ወደ አዲስ ምእራፍ እየወሰዳቸው ነው።

አሁን የልማት ድርጅቶቹ ከኪሣራ ወጥተው ለሀገር ረብጣ ገቢና ከፍተኛ ትርፍ እያስገኙ ነው። ተረስተውና ተጥለው የነበሩ ታሪካዊ ቅርሶች፣ ተጠግነውና ተሻሽለው ለጎብኝዎች ክፍት ሆነዋል። ከዚህ በፊት አይተናቸው የማናውቅ የሀገራችን ሀብቶችም እንደ አንድነት ፓርክና እንደ ታችኛው ቤተ መንግሥት ያሉት ታድሰውና ለነገው ዘመን ተዘጋጅተው ተጨማሪ ሀብት ማመንጨት ጀምረዋል።

በሪፎርም መሥመር ውስጥ የገቡት የልማት ድርጅቶችና ታሪካዊ ቅርሶች ብቻ አይደሉም። ዛሬ ከተማና ገጠሩ እኩል እየተቀየረ ነው። የኮሪደር ልማት የከተሞቻችንን ገመና ገላልጦ አሳይቶናል። በስመ ከተማ ኢትዮጵያን የሞሉት መኖሪያ፣ መናኸሪያ እና መገናኛ ያልሆኑ ከተሞች ነበሩ። ሕይወት በሰቆቃ የሚገፋባቸው የመከራ ዳሶች፤ ንግድ፣ ሥራና አገልግሎት የማይሣለጥባቸው መተራመሻዎች፤ ፋይናንስ፣ ትራንስፖርት፣ ኔትዎርክ፣ መዝናኛና ታሪክ የማይተሣሠርባቸው መንደሮች እንደነበሩን የኮሪደር ልማት ገልጦ አሳይቶናል።



ከተሞቻችን የዘመናዊ ከተማ መልክ ለመያዝ ጥረት ማድረግ ጀምረዋል። ለመኖሪያ የተመቹ፣ ለንግድና ለኮንፈረንስ የተስማሙ፣ ቢያስጎበኟቸው የማያሳፍሩ፣ ተምሳሌት ተደርገው የሚጠቀሱ እየሆኑ ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ **"የአፍሪካ ውብ አበባ"** ተብላ ብትጠራ፣ እውነታ እንጂ ባዶ ሙገሳ ተደርጎ አይወሰድም። በአረንጓዴ ዐሻራ 56 ቢልዮን ችግኞችን ስንተክል የተራቆቱ መሬቶቻችን አረንጓዴ ለበሱ፤ ተጠራርጎ የሚሸሸውም አፈር ባለበት ተገደበ።

የበጋ መስኖ ልማት የኢትዮጵያን የስንዴና ሩዝ ታሪክ ቀየረው፤ የሌማት ትሩፋት የወተት፣ የዶሮና የዕንቁላል ምርታችንን ጨመረው፤ ይሄም በምግብ ራስን የመቻል ግብ ሩቅ እንዳልሆነ ጠቁሞናል። መሶብ የኢትዮጵያን የአገልግሎት አሰጣጥ መልክ ሲያስተካክለው፤ ፋይዳ አዲሱን ዲጂታል ማንነት ሲያጠናክረው፤ የወንዝ ዳር ልማት የኢትዮጵያን የውኃ ዕሳቤ ሲቀይረው፤ የገበታ ፕሮጀክቶች የኢትዮጵያን ነባር መልኮች በአዲስ መልኩ ሲገልጡ - በዓይናችን አይተናል። የአዲስ አበባ ለውጥ የዓለም ጉባኤዎችን "ኑ ወደ እኔ" እያለ ሲጣራ፣ ኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የምርት ባህላችንን ሲያድሰው ፣ የማዕድን ልማታችን የዘመናት የወጪ ንግዳችንን በአጭር ጊዜ መብለጥ ሲችል - ለመታዘብ በቅተናል። እነዚህን ተስፋ ሰጪ ጅማሮዎች አጠናክረን እንቀጥላለን።

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣**
**የተከበራችሁ የሀገራችን ሕዝቦች፣**



ባለፉት ዓመታት የመጣንበት መንገድ እንደ ኮሪደር የተስተካከለ፣ እንደ ወንዝ ዳር ልማት ያማረ ብቻ አልነበረም። ብዙ ፈተናዎችን አልፈናል። የኢትዮጵያ ለውጥ ያስደነገጣቸው አካላት በክፉ ዓይናቸው ያዩን ጀመር። ይህች ሀገር እንዴት እንደተነሣች፣ ለምን እንደተነሣች እና የት ለመድረስ እንደተነሣች ገብቷቸዋል።

ይህች ችግኝ ዋርካ ከሆነች፣ በኋላ አንችላትም ብለው ሠጉ። ስለዚህ፣ **"ባልበላው ጭሬ አፈሰዋለሁ"** በሚለው የደካማዋ ዶሮ መንገድ ተነሡ።

ዘሩ ሳይበቅል በፊት፣ ቡቃያው ከማፍራቱ አስቀድሞ፣ ሰብሉ ደርሶ መታጨድ ሳይጀምር - ማጨናገፍ አለብን ብለው ተንቀሳቀሱ። ከሮጠች አንይዛትም ብለው - የመጨረሻውን ጥይታቸውን መተኮስ ጀመሩ። ባዳና ባንዳ ለእኩይ ዓላማ ተባበሩ። የውጭ ላኪና የውስጥ ተላላኪ ተቀናጅተው ተነሡ።
ሀገር ሻጭና ሀገር በታኝ ቀብድ ተቀባበሉ። ብዙ ሞከሩን፤ ብዙ ፈተኑን፤ ብዙ ደከሙ፤ ብዙም ተሟሟቱ። በነጠላም በድርብም ታገሉን። በግንባርም፣ በሚዲያም፤ በሰይፍም፣ በሰልፍም፤ በውሸትም በሐሜትም፤ በተንኮልም በሸረባም - በአገኙት የትግል ሜዳ ሁሉ ከጉዟችን ሊያደናቅፉ መከራቸውን አዩ። ኢትዮጵያን ግን አልቻሏትም። ውድቀቷን ሲመኙ ትነሣለች፣ ድክመቷን ሲናፍቁ ጠንክራ ትወጣለች ፣ ተበተነች አለቀላት ብለው ሳይጨርሱ ተሰብስባ ትገኛለች። **የኢትዮጵያ ነገር ትንግርት ነው።**

**መወየቧን ለጠብቁ ፍካቷን፣ ድህነቷን ለሚሹ ዕድገቷን፣ አዝጋሚ ርምጃዋን ለቋመጡ ፈጣን ሩጫዋን እያሳየች፤ ከታሪክ መሠረዝዋን ሲጠብቁ ታሪክ እየሠራች፤ በእመርታ ወደፊት ቀጥላለች!**

ያለፉት ዓመታት የመደላድል ዓመታት ነበሩ። ሰንኮፉን ለመንቀል፤ አረሙን ለማረም፤ ዕንቅፋቱን ለማንሣት፤ መንገዱን ለመጥረግና መሠረቱን ለመጣል የታገልንባቸው ዓመታት ነበሩ። መንገዳችን ቀና፣ ዓላማችን ሁነኛ፣ መዳረሻችን አመርቂ፣ አካሄዳችን ትክክል መሆኑን ሠርተን አረጋግጠናል። በዕንቅፋቶች ሳይወድቅ፣ ተገቢውን ምላሽ እየሰጠ የሚሄድ፤ አይበገሬ የፖለቲካል ኢኮኖሚ ሥርዓት እየገነባን መሆኑን በተግባር አረጋግጠናል። ኮቪድ መጥቶ ዓለም ሲዘጋ በጽናት ቀጥለናል። ዘመቻ ተከፍቶብን ሳለ፣ ዓለም ጀርባውን ሲያዞርብንና ፍርደ ገምድልነቱን ሲያሳየን ፣ ለሴኮንድ ሸብረክ አላልንም። በወንዛችን የመጠቀም መብታችንን ለማስከበር ደፋ ቀና ስንል፤ ግድባችንን ከፍጻሜ እንዳናደርስ፣ በረጅም ገመድ አሥረው ሲጎትቱን **ተንገዳገድን እንጂ አልወደቅንም።**



በምግብና በወሳኝ ምርቶች ራሳችንን ለመቻል፤ በእግራችን ለመቆም የምናደርገውን መውተርተር ሲሳለቁበት - አንገት ደፍተን አልቀረንም። በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ውስጥ፤ የአይበገሬነታችንን መጠን ያወቅነው፣ ከመጽናት ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለን የተረዳንበት ጊዜ ነው።

የዚህና የመጪዎቹ ፓርላማዎች ድርሻ የኢትዮጵያን ሥልጣኔ መገንባት ነው። ኢትዮጵያ የብዝኃ ሥልጣኔ ሀገር ናት። ፈር ቀዳጅ የሆንባቸው፤ ለብዙዎች መነሻ ተደርገን የምንታይባቸው፤ የአስደናቂ ታሪኮችና ዕሴቶች መገኛ ምድር ሆነን ሳለ፣ እንደ ሀገር አንድ ትልቅ ውሱንነት አለብን የማስቀጠል ፈተና ደግሞ ደጋግሞ ይገጥመናል። እንጀምራለን፤ ነገር ግን አናስቀጥልም። እንመሠርታለን፤ ነገር ግን ገንብተን ሳንጨርስ ቀልባችን በሌላ ነገር ይጠመዳል። የዘራነውን ሳናጭድ፤ የወቃነውን ሳናበጥር፤ ያመረትነውን ጎተራ ሳናስገባ፤ በሂደቱ መሐል እንጠፋለን። አባት የጀመረውን ልጅ መጨረስ ሲሳነው እንደማየት ያለ እርግማን የለም። አንዱ ትውልድ የሰበሰበውን ሌላኛው እየበተነው አንዱ የገነባውን ሌላኛው እያፈረሰው መነሻ ወረት ሳይጠፋ ከባዶ እየጀመርን መሠልጠን የሚባል ነገር ከቶ አይታሰብም። በእነዚህ ተቃርኖዎች ምክንያት፤ ሀገራችን ዕምቅ ሀብት እያላት፤ ለድህነት ተዳርገናል። የዘመናት ሥልጣኔ እያላት፤ ሀገረ-መንግሥቷ በቅቡልነት ፈተና ደጋግሞ ይመታል።

በቅኔ ጭምር ተነጋግረን የምንግባባ ሕዝቦች፥ ሐሳብን በጠመንጃ ፍላጎትን በሽፍትነት ለመግለጽ ዛሬም ይዳዳናል። ለሌሎች የሚተርፍ የኢነርጂ ምንጭና የውኃ ሀብት እያለን፥ ኤሌክትሪክና መጠጥ ውኃ ገና በየቤታችን አልደረሰም። ኢትዮጵያ፥ አንድ አህጉር ሊመግብ የሚችል የእርሻ መሬት ይዛ፤ ለዓለም ሕዝቦች አያሌ የሰብል ዓይነቶችን ያስተዋወቀ የግብርና ታሪክ እያላት፤ በምግብ ራሷን ለመቻል ግን፣ ገና ፈተና ሆኖባታል።

ቀጣዩ የኢትዮጵያ ሥልጣኔ እነዚህን ተቃርኖዎች የሚፈታ መሆን አለበት። ቀደም ብለን ያነሣነውን በዓለምና በቀጣናችን የሚካሄደውን የለውጥ ንቅናቄ መበየንና መወሰን የምንችለው፣ የራሳችንን ሥልጣኔ በራሳችን መንገድ መገንባት ስንችል ብቻ ነው። ግባችን ድህነትን ማሸነፍ፣ ሥራ መፍጠር፣ የቤት ችግርን ማቃለል፣ ትምህርትና ጤናን ማዳረስ፣ ለኢንቨስተሮች ብድር ማመቻቸት፣ ቀልጣፋ ትራንስፖርት መዘርጋት፣ መብራትና ውኃ ማስገባት ብቻ አይደለም። እነዚህ ሁሉ መንገዶች እንጂ መዳረሻዎች አይደሉም። የእህሉ መሰብሰብ፣ መፈጨት፣ መቦካትና መጋገር የአንድን ሰው ረሃብ አያስታግሠውም። ምግቡ ገበታው ላይ ቀርቦ መበላት አለበት። ከላይ የጠቀስኳቸው ተግባራት ሁሉ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያንን ዘላቂ ችግሮች እስከወዲያኛው አይፈቱትም።




ይህ እንዲሳካ ደግሞ እንደ ሀገር፥ ሁላችንም ወገባችን አሥረን፣ ስሜታችንን ገርተን፣ ጥሪታችንን ቋጥረን፣ ዐቅማችንን ሰብስበን፣ ትኩረታችንን በግዙፍ ግቦቻችን ላይ አድርገን  አዲስ ኢትዮጵያዊ ሥልጣኔን ለመገንባት ቆርጠን መነሣት ይኖርብናል። ሰዎች፣ መሬት ትንሽ መሆኗን፣ በንድፈ ሐሳብ ያወቁትን በተግባር ያረጋገጡት፣ በመንኮራኩር ወደ ላይ ሲወጡ ነው። ያቺ ቢልዮኖችን የያዘችው መሬት፣ ከምንኖርበት ጋላክሲ አንፃር ትንሽ መሆኗንም ተገነዘቡ። እኛም ወደ ላይ ከፍ ብለን ካላየን የመንደርና የሠፈር ጉዳዮች ግዙፍ ይሆኑብናል። በጠባብ ኩሬ ላይ እንደሚዋኝ ዓሣ፥ ግዝፈትና ዕሳቤያችን ከዕለት ወደ ዕለት እያነሰ ይሄዳል። ስለዚህ መፍትሔው ጠባቡን ኩሬ በሰፊው ውቅያኖስ መተካት ነው። በሚመጥነን ሰፊ ባሕር ውስጥ ለመዋኘት አቋምና ቁመናችንን አስተካክለን መገኘት ይጠበቅብናል።

ሌላኛው ወሳኝ ጉዳይ፣ ሰፊውን ባሕር ስለመቅዘፍ ስናስብ፣ ወደሚፈጠረው የዓለም ሥርዓት መሰስ ብሎ መግባት አይደለም። ተቀላቅለን የምናመጣው አዎንታዊ ለውጥ መኖር አለበት። በዓለም ረዥሙ ወንዝ ዓባይ፣ ከመነሻው እስከ መድረሻው ጨው የሌለው ንጹሕ የሚጠጣ ውኃ ነው። ወደ ሜዲትራንያን ሲቀላቀል ግን ይቀየራል። ጨዋማው ውኃ ንጹሕ ከመሆን ይልቅ፣ ግዙፉ ዓባይ፣ ባሕር ውስጥ ገብቶ ጨዋማ ይሆናል።

እኛ ግን ወደ ዓለም ስንገባ ትልቋ ኢትዮጵያ ትንሽ እንድትሆን አንፈልግም። ማንነቷን ያጣች ሀገር እንድትሆን አንሻም። ፍላጎታችን ኢትዮጵያ በዓለም እንድትለወጥ ሳይሆን፤ ራሷም ገዝፋ ዓለምን እንድትለውጥ ማድረግ ነው። እዚህም እዚያም ከሚፈጠሩ ችግሮች ተነሥተን፤ ከዕለት ተዕለት ፈተናዎቻችን አንጻር መዝነን እና በየጊዜው የምናስተናግዳቸውን እኩይ ገጠመኞች አስበን ስናየው፣ ይህ የምናወራው ነገር የማይሳካ ሕልም ሊመስል ይችላል። ቅዠት ግን አይደለም። ሕልማችንን ወደ ተግባር የሚቀይሩትን ልበ ብርቱዎች ካገኘ፣ እውን የሚሆን ራዕይ ነው። ተኝተን ያለምነው ሳይሆን፤ - ዐቅደን የነደፍነው ብርቱ ራዕይ። ታሪክ የሚቀይር ኢትዮጵያዊ ራዕይ።

ሰዎች ዓለም ክብ ናት ሲሉ፤ ሰዎች ምድርን ለማሰስ ሲነሡ፤ ሰዎች ጨረቃን ለመርገጥ ሲጓዙ፤ ሰዎች አውሮፕላን ሲሠሩ፤ ሰዎች ስልክን ለመፍጠር ሲሞክሩ - ሁሉም ሕልመኞች ተብለው ነበር። **ዛሬ የእነርሱ ሕልም እውን ሆኖ፣ ትውልድ እየኖረው ነው።** የእኛንም ሕልም፣ ልጆቻችን በተግባር የሚኖሩት የተስፋ አድማስ ነው። ባለፉት ዓመታት የመጣንባቸው መንገዶች፣ በልበ ሙሉነት ከተጋን ሕልማችንን መኖር እንደምንችል በተግባር አረጋግጠውልናል። የምግብ ሉዓላዊነትን ለማረጋገጥና ሀገራችንን ከልመና ለመታደግ የበጋ ስንዴ ልማትን ስንጀምር ሕልመኞች ተብለን ነበር። ዳሩ ግን፣ ጅማሮአችን ገና ከአሁኑ፣ ከውጭ የሚገባውን **ስንዴ ማስቀረት ችሏል**። ከተሞቻችንን ስለማዘመን ዐቅደን "ኮሪደር እናልማ" ስንል ብዙዎች ተሳልቀውብን ነበር። ዳሩ ግን፣ በአጭር ዓመታት ውስጥ፣ የከተሞቻችን ለውጥ፣ ከአህጉር ተሻግሮ የብዙዎች መነጋገሪያ ለመሆን በቅቷል።

ለዘመናት ያንቀላፉ ታላላቅ ፕሮጀክቶችን ለመቀስቀስ ስንነሣ - የቅዠት ያህል ተቆጥሮ ነበር። ዳሩ ግን፣ ሕልማችን ሕዳሴን ከሞት ቀሰቀሰ፤ እነ መገጭና ርብ ግድቦችን ከተኙበት አስነሣ፤ ጣና በለስን ወደ ምርት አስገባ። ኢትዮጵያ ልትፈርስ ነው እያተባለ ከበሮ ሲደለቅ፣ "ኢትዮጵያ በአንድነት ትዘልቃለች" ስንል ፕሮፓጋንዳ የመሰላቸው ነበሩ። ዛሬ ግን የጠላቶቻችን ጭንቀት ኢትዮጵያን በቀይ ባሕር እንዳትነግሥ መገደብ ሆኗል። ገዥ ፓርቲና ተፎካካሪዎች ለአንድ ሀገር በአንድ መንግሥት ውስጥ ሲሠሩ፣ ያልተስማማቸው ነበሩ። ለብሄራዊ ጥቅም በጋራ መስራት እንደሚቻል በተግባር አሳይተናል። ዜጎቻችንን **"ዋና እና አጋር"** እያለ ደረጃ የሚመድበውን ኋላቀር ዕሳቤ ስናፈርሰው የተሳለቁብን ነበሩ። ዛሬ ግን፣ ባላንጣዎቻችን፣ ከፋፍለው ሊያጠቁን ሲከብዳቸው፣ ለክፋት እነርሱ ተጣመዱ።

አሁንም "አዲሱን የኢትዮጵያን ሥልጣኔ እንገነባለን" ስንል፣ ተራ ፉከራ አይደለም - በተግባር የሚገለጥ የትውልድ ቃል ኪዳን ነው። በተጨባጭ የሚሳካ፤ ሀገር ወዳድ ሁሉ የሚኮራበት ግዙፍ ሕልም ነው። ጥያቄው፣ **"ይቻላል ወይስ አይቻልም?"** የሚለው አይደለም። እንደሚቻል እርግጠኞች ነን። ምናልባትም፣ ትንታኔ የሚያሻው **"የምናሳከው እንዴት አድርገን ነው?"** ለሚለው ጥያቄ ነው። በመደመር ዕሳቤ ተጉዘን እንደምናሳካው ስንናገር ቅንጣት ጥርጣሬ የለንም።

ዕምቅ ዐቅሞችን ዐውቀን ፣ አካሄዳችንን ገቢር ነበብ አድርገን ፣ ከዓለም ተመክሮ ወስደን በኅብረ ብሔራዊ አንድነት ላይ ጸንተን ፣ የቡድንና የግል መብትን በሚዛን ጠብቀን ፣ አዲስ ሲቪክ ማንነትን ገንብተን ፣ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ምኅዳርን በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ላይ አጽንተን የኢትዮጵን ሕልሞች እናሳካለን። መንግሥት፣ መንገድ ቀያሽም ተሳታፊም በሆነበት የኢኮኖሚ ሥርዓት፣ ሀገራዊ ሀብታችን ይደረጃል። በምክክር፣ በድርድርና በፍትሕ ሥርዓት ሰላማችን ይጸናል በአረንጓዴ ዐሻራ የሥነ ምኅዳራችን ጤናማነት ይጠበቃል ዘላቂ ሥነ ምኅዳር እየፈጠርን ከትውልድ በአደራ የተረከብነውን ሀገር አሻሽለን በማስቀጠል፤ የኢትዮጵያን ሥልጣኔ እንገነባለን።

## ውድ ኢትዮጵያውያን፣
## የተከበራችን የምክር ቤት አባላት፣

በቀጣዩ ጊዜያት በሀገራዊ ምክክር ምክረ ሐሳቦች መሠረት የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ይኖረናል። የፖለቲካ ምኅዳራችን በትብብርና በፉክክር ሚዛን ላይ ተመሥርቶ እንዲቀጥል ይደረጋል። ከተፎካካሪ ፓርቲዎች በተለይም በምርጫው ንቁ ተሳትፎ ከነበራቸው ፓርቲዎች ጋር አብሮ ለመሥራት መንግሥት ዝግጁ መሆኑን በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እወዳለው። የተጀመረው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ መሬት ረግጦ የታለመለትን ግብ እንዲመታ ይደረጋል። ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል ያለበት የበጀት አካሄድን እንከተላለን።

ለኅብረ ብሔራዊ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ወሳኝ የሆነው፣ የወል ትርክት ግንባታ ተገቢውን ትኩረት ያገኛል። ምርታማነት ባህልም፣ ሥርዓትም እንዲሆን ይሠራል። የሰላም ሁኔታችንን የበለጠ ለማጽናት የውይይትንና የይቅርታን መንገዶች እንከተላለን። በሌላም በኩል ደግሞ፤ የተጠናከረ የጸጥታና የደኅንነት ዝግጅት፣ ክትትልና ሥምሪት ይኖረናል። የሚዲያ ምኅዳሩ፥ ሕግን፣ ሀገራዊ ዕሴቶችንና ፍላጎቶችን ባከበረ መልኩ እንዲንቀሳቀስ ይደረጋል። ሙስናንና ሌብነትን፤ የዘመድ አሠራርንና ወገንተኝነትን ለማስወገድ፤ መንግሥት **መረር ያሉ ርምጃዎችን ይወስዳል።**

እንደ መሶብ ያሉ ዘመናዊ አሠራሮችን እስከታችኛው እርከን በማድረስና የተጀመረውን የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም በማጠናከር፣ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲዘምን ይደረጋል። የመኖሪያ ቤት ችግሮችን በመሠረታዊነት የሚፈቱ አዳዲስ አካሄዶችን እንከተላለን። ከዚህ በፊት ያገኘናቸውን ተሞክሮዎች መሠረት በማድረግ፤ የመንግሥት ፕሮጀክቶች ጊዜና ገንዘብ በሚቆጥብ የፈጠራና ፍጥነት አሠራር ይከናወናሉ። የትምህርት ጥራትን የበለጠ በማስቀጠል የኢትዮጵያን ሥልጣኔ የሚገነባውን ትውልድ ለመፍጠር አበክረን እንሰራለን።
ኅብረተሰቡ በሞራል፣ በዕሴት፣ በክሂሎትና በባለቤትነት መንፈስ የሚታነጽበትን መንገድ እንከተላለን። ኢትዮጵያ ለድርቅ፣ ለጦርነት፣ ለሉላዊ የኢኮኖሚ ቀውሶች፣ ለጂኦ ፖለቲካዊ ፈተናዎች እና ለማናቸውም ችግሮች የማትበገር እንድትሆን የሚያስችላትን ሁለንተናዊ የዝግጁነት ሥርዓት እንገነባለን። የሲቪል ሰርቪስ አሰጣጥ በሂደቱ ሳይሆን በውጤቱና በተጽዕኖው እንዲመዘን ይደረጋል።

ባህልና ሥነ ጥበብ ለሀገረ መንግሥት ግንባታ፣ ለሕዝቦች ትሥሥር እና ለኢትዮጵያ ብራንድ ግንባታ ተገቢውን ሚና ለመጫወት በሚያስችላቸው መንገድ ይደገፋሉ። የዳያስፖራው ማኅበረሰብ በሀገሩ ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ኑሮ፤ አዎንታዊ ሚና እንዲጫወት፤ ትረት ይደረጋል። የውጭ ግንኙነታችን የኢትዮጵያን ተጽዕኖ በዓለም ላይ ሊያሳይ በሚችል መልኩ እንዲቃኝ ይደረጋል። ከሁሉም የዓለም አካላት ጋር ብሔራዊ ጥቅማችንን መሠረት አድርገን አብረን እንሠራለን። ጎረቤቶቻችን በተፈጥሮ ያገኘናቸው ወዳጆቻችን ናቸው። በመሆኑም ከጎረቤቶቻችን ጋር በሰላም፣ በጋራ ጥቅም እና በትብብር የመሥራት መርሐችንን እንገፋበታለን።

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ያለ **ባሕር በር** እውን ሊሆን አይችልም። በመሆኑም በሰጥቶ መቀበል መርሕ ኢትዮጵያ ወጥቶ መግቢያ በር እንዲኖራት ተግተን እንሰራለን። የኢትዮጵያን ታላቅነት፣ የዓለምንና የአካባቢያችንን ወቅታዊ ሁኔታ፣ ብሎም የወደፊቱን የዓለም አካሄድ ያገናዘበ የመከላከያ ኃይል እንዲኖረን እንሠራለን። በቀጣናችን፣ የአየር የበላይነትን ለመፍጠር የሚያስችል ዐቅም እንገነባለን። የሚኖረን መከላከያ - ዘመናዊ፣ ፈጣሪ፣ ሁሌም ዝግጁ፣ ብቁና ንቁ፤ በየዐውዶቹ የመሠማራት ዐቅምና ቁመና ያለው ይሆናል። ችግሮች ሳይፈጠሩ በፊት አስቀድሞ ማወቅና መግታት፤ ከመጡም መከላከል፤ ከባሰም ማሸነፍ የሚችል ኃይል ሆኖ ይገነባል። የሃይማኖት፣ የሲቪክና የባህል ተቋማት ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል።

የኢትዮጵያ ሃይማኖቶች የተገነቡበት መንፈሳዊ ዕሴት፣ ለሀገረ መንግሥት እና ለዕሴት ግንባታ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሙስናን፣ ብልሹ አሠራርንና ከሥነ ምግባር የወጡ አካሄዶችን ለማረቅ ፍቱን መድኃኒት ነው። በሕዝቦች መካከል ወገን ዘለል ትሥሥር ለመፍጠርም ዐቅም አለው። የሲቪክ ተቋማት፣ በሀገር ፍቅር መንፈስ ተቃኝተው፣ ሲቪክ ማንነትን በመገንባት ረገድ እስካሁን ካበረከቱት በላይ እንዲያበረክቱ ይደረጋል።

እነሆ ታሪክ ምርጥ የሆነ ዕድል ከፊታችን ዘርግቷል። ኢትዮጵያን ትልቅ ብቻ ሳትሆን ታላቅ የማድረግ ዕድል ተሰጥቶናል። የኢትዮጵያን አዲስ ሥልጣኔ የመገንባት ዕድል በእኛ ዘንድ አለ። ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት ያላት ኅብረ ብሔራዊ አንድነቷ የጸና ምርታማነትን ባህል ለማድረግ የምትተጋ መሪና ፈር ቀዳጅ የሆነች አይበገሬ ኢትዮጵያን የመገንባት ታሪካዊ ዕድል ከፊታችን አለ። ይሄንን ታሪካዊ ዕድል ከትጋት ጋር ደምረን እንድንጠቀምበት በጫካ ያላችሁ ወገኖች ወደ ሰላማዊ መንገድ ኑ! ያኮረፋችሁ ወገኖች የይቅርታን መንፈስ ተላብሳችሁ፣ በሀገር ግንባታ ተሳተፉ! ተፎካካሪ ፓርቲዎች በብሔራዊ ጥቅም ላይ በጋራ ለመቆምና በአማራጭ ሐሳቦች ለመፎካከር ተነሱ! የዛሬ ወጣቶች በአርቆ አሳቢነት ነጋችሁን ቅረጹ። **የትናንት ወጣቶች** ካለፈ ስህተታችሁ ተማሩ፤ ከአብዮታዊ የትግል ስልት ራቁ፤ የተጣሉትን አስታርቁ፤ የሸሹትንም መልሱ። የዛሬ ልጆች በዕውቀት፣ በክህሎትና በሥነ ምግባር ታንጻችሁ ኢትዮጵያን ለመውረስ ተሰናዱ! የሀገር አባቶችና እናቶች ለነገዋ ኢትዮጵያ ታላቅነትና ሥልጣኔ ጸልዩ ታሪካችሁን አውርሱ ትውልዱንም ገንቡ። **ሁሉም ዜጋ በተሠፈረለት ጊዜ፤ በላብና በዕውቀቱ፤ የመደመርን ሥልጣኔ እውን ለማድረግ ይትጋ!!**

ትናንት አልፏል ነገም ገና አልደረሰም -ዛሬ ግን ምቹ ሆኖ ቀርቧል። ዛሬን ከሠራንበት ትናንትን ማስተካከል ይቻላል። ዛሬን ከሠራንበት ነገን መተንበይ ብቻ ሳይሆን፣ በፈለግነው ዓይነት መንገድ መቅረጽ እንችላለን። ይህ ፓርላማ በሚኖረው ቆይታ ዝርዝር ጉዳዮችን ከመጠየቅ ባሻገር፣ “የሚሠራው ሥራ የሕዝቡን ሕይወት ምን ያህል ለወጠ? የመደመር ሥልጣኔስ ምን ያህል ተሳካ?” የሚለውን እንዲከታተል አደራ ለማለት እወዳለሁ። በመጨረሻም፣ ባለፉት ዓመታት ያሳካናቸው ውጤቶች እንዲመጡ የበኩላቸውን ሚና ለተጫወቱ አካላት ሁሉ፣ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ። የአመራር መግባባት በሌለበት፣ የሥራ ባልደረቦች ባልተባበሩበት፣ ያለ አጋር አካላት ቀናኢ ድጋፍ እና ያለ ሕዝብ አስተዋጽኦ የተፈጠረው ባልተፈጠረ፣ የተሳካው ባልተሳካ ነበር። እንዲሁም፣ አብሮነታቸው እና ድጋፋቸው ያልተለየኝን ውዷን ባለቤቴንና ልጆቼን በዚሁ አጋጣሚ ከልቤ ለማመስገን እወዳለሁ።

**መልካም የሥራ ዘመን ይሁንልን!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**አመሰግናለሁ!!**



## የመደመር መንግሥት ምስረታ

መስከረም 25 ቀን 2019 ዓ.ም